ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ

25 ኖቬምበር 2020

ለዓለም ባሃኢዎች

እጅግ የምትፈቀሩ ወዳጆች፥

“በተጨባጩ ዓለም አካል ውስጥ የሚነዝረውን” እና በአማኞች መካከል ዘላቂ የፍቅር ትስስሮችን የሚያራምደውን ያን ኃይል፣ የቃል ኪዳኑን ኃይል፣ የማሰቢያ አጋጣሚ በሆነው በዚህ ልዩ ቀን በጥልቅ ፍቅር ሠላም እንላችኋለን። ከሪዝቫን ወዲህ ባሉት ወራት፥ በሁሉም ቦታዎች ያሉ ወዳጆች፥ በእምነቱ ተቋማት በብቃት እየተመሩ፥ በእያንዳንዱ አህጉር እና ሃገር፥ የምትሰቃይን ዓለም ፍላጎቶች ለማሟላት፥ ፈጠራ እና ቁርጠኝነት መለያቸው የሆኑ ጥረቶችን ሲያደርጉ፥ በባሃኦላህ ተከታዮች የተዋሃደ እንቅስቃሴ ውስጥ የዚህን ጠንካራ ኃይል ማስረጃዎች ተመልክተናል። በሁሉም ፈተናዎች ውስጥ የፀናው አይበገሬነታችሁና በዙሪያችሁ ላሉት ደህንነት ያላችሁ የማይናወጥ መሰጠት በታላቅ ተስፋ ሞልቶናል። ነገር ግን፥ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ፥ ተስፋ የተሚጠጠ ሀብት መሆኑ አይደንቅም። ከፊት ለፊታችን ያሉት አስርተ ዓመታት፥ የሰው ዘር ቤተሰብ ከዚህ ቀደም ከተጋፈጣቸው ተግዳሮቶች ሁሉ እጅግ አስጊ የሆኑትን ይዘው ለመምጣት የተዘጋጁ ስለመሆኑ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ያለው ግንዛቤ እየገዘፈ መጥቷል። በሕይወቶች እና በመተዳደሪያዎች ላይ የሚያስከፍለው ዋጋ ክብደት መጨረሻው ገና ያልታወቀው አሁን ያለው ሉላዊ የጤና ቀውስ እንዲህ ካሉት ተግዳሮቶች መካከል አንዱ ብቻ ነው፤ እርስ በእርስ እና በሰፊው ማሕበረሰብ ውስጥ ያሉትን እህቶቻችሁንና ወንድሞቻችሁን ጭምር ለመርዳትና ለመደገፍ የምታደርጓቸው ጥረቶች በእርግጥ ቀጣይነት ሊኖራቸውና በአንዳንድ ቦታዎችም ሊስፉፉ ይገባል።

የእምነቱ መርከብ፥ ቁጡ ማዕበሎች የሰው ዘርን እያናወጡት ባሉበት ከዚህ ወቅት ዳራ፥ በተቃራኒው ፥ ወደ የባሃኢ ዘመን ሶስተኛው ምዕተ ዓመት የሚያሻግሩትንና የእምነቱን ሕብረተሰብ የመገንባት ኃይል ዕውን ለማድረግ የባሃኢ ማህበረሰቡን አቅም በጉልህ ሁኔታ የሚያጠናክሩትን ተከታታይ ዕቅዶች ለመጀመር እየተዘጋጀ ነው። እንደምታውቁት፥ እነዚህን አዲስ ተከታታይ ዕቅዶች የሚያስጀምረው የመጀመሪያው ዕቅድ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ያህል ብቻ ነው። ብሔራዊ ማህበረሰቦች እንዳሰቡት ከሪዝቫን 2021 በፊት ብዛት ያላቸውና የተፋጠኑ የእድገት መርሃግብሮችን ለማቋቋም ሁኔታዎች በሚገቷቸው ቦታዎች፥ የሚቀጥሉት አሥራ ሁለት ወራት ሥራቸውን ለማስቀጠል ተጨማሪ ጊዜ ይሰጧቸዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ የእድገቱ ሂደት በተፋጠነባቸው ሁሉም አካባቢዎች፥ ዓመቱ፥ እያደገ የሚሄድ ቁጥር ያላቸው ነፍሶችን በከለላ ጠለላነቱና በሁሉን አቃፊነት አመላካከቱ በሚታወቀው የባሃኢ ማህበረሰብ እቅፍ ውስጥ ለማስገባት የሚያስችላቸውን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች እያዳበሩ፥ በተያዘው ዕቅድ የተገኙትን ስኬቶች ለማጠናከር ዕድል ይፈጥራል። በአገር፣ በክልል እና በስብስብ ደረጃዎች የተረጋገጠ ጥንካሬዎችን ያስመሰከሩ ማህበረሰቦች በበኩላቸው አነስተኛ ልምድ ያሉባቸውን አካባቢዎች ሲያግዙና ሲረዱ ማየት እንሻለን። በዚህ የዓመት ሙሉ እንቅስቃሴ ወቅት፣ እያንዳንዱ ማህበረሰብ እስከ አሁን በሥራ ላይ ያልዋለ የታመቀ አቅም ካለው አውጥቶ በመጠቀም እድገቱን የሚያደናቅፉትን ማናቸውንም መሰናክሎች ለማለፍ መነሳትና ወደፊት ለሚመጡት ፍላጎቶች መዘጋጀት ይኖርበታል። እነዚያ መሠረታዊ ንጥረ ነገሮች አጅግ ጎልቶ በሚታይ መልኩ በመተሳሰርና በመዋሃድ የህብረተሰቡን ኃይሎች በመስክ ድርጊት የሚያበራክቱት፥ በማበብ ላይ በሚገኝ ማህበረሰብ አውድ ውስጥ፥ በተለይም በአንድ መንደር ወይም ሰፈር ውስጥ ባለ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በሚደረግበት ማዕከል ውስጥ፥ እና እያንዳንዱ የእቅዱ ማዕቀፍ ንጥረ ነገር የሚጠይቀውን ያህል ትኩረት ሲሰጠው ነውና፡፡

መጪው ዕቅድ፥ በሁሉም ቦታዎች በሚገኙ ስብስቦች ውስጥ ለዕድገት የሚያስፈልገውን ከመስጠት ባሻገር፥ ማህበረሰቡ የአብዱል-ባሃን ዕርገት መቶኛ ዓመት ለማክበር በሚዘጋጅበት ወቅት፤ በአብዱል-ባሃ ሕይወት ብሎም እርሱ ማዕከል በሆነበት የቃል ኪዳኑ ጥንካሬ ላይ ጥልቅ ማሰላሰል የሚደረግበት ዓመት ይሆናል። የዚህ ምዕተ-ዓመታዊ በዓል መከበር ያለጥርጥር ግለሰብ አማኞችንም ሆነ ማህበረሰቡን እርሱ የአምላክ ምስጢር የሆነው ከዚህ ዓለም ያለፈበትን እጅግ በጣም አሳዛኝ ወቅት አንድምታ ላይ በጥልቀት እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። የእርሱ ማለፍ በዚያን ዘመን ለሚኖሩ ባሃኢዎች የጥልቅ ፍቅራቸውና ታማኝነታቸው ዓላማና ተምሳሌት የሆነውን ነፍጎአቸዋል፤ ለዚህ ዘመን ታማኞች፣ እስካሁንም እርሱ አቻ የሌለው ነው፡- አባቱ ያስተማረውን ሁሉ በቃልና በተግባር በፍፁምነት የተላበሰ፣ በእርሱም አማካይነት የባሃኦላህ ቃል ኪዳን “መታወጅ፣ መበረታትና መረጋገጥ” የተቻለበት ነው። በተጨማሪም መጪው ዓመት የእርሱ “ወሳኝ”፣ “ታሪካዊ” እና፣ “የማይሞተው” ሰነድ፣ በቃለ-

ኑዛዜውና ቃል ኪዳኑ አማካኝነት ጥሪውን ያሰማበት፤ የአስተዳደሩንም ሥርዓት ባህሪያት በዝርዝር ያስቀመጠበትና፣ ያ “ሁሉን ቻይ የሆነው የባሃኦላህ ሕግ በምድር ላይ እንዲመሰረት የቀየሰው የመለኮታዊ ሥልጣኔ ንድፍ” ወደ እንቅስቃሴ ያስገባበት አንድ መቶኛ ዓመት የሚታወስበት እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህ “ልዩ” እና “በመለኮት የተፀነሰ” ሥርዓት፣ ይህ “ኃያል የአስተዳደር መዋቅር” ቃል-ኪዳኑን ለማስቀጠልና እና የዕምነቱን መንፈሳዊ ኃይል ለማሰራጨት፡ በእርሱ በመለኮታዊው መሀንዲሱ (አርክቴክቱ) የተቀረጸ ነው። በሚቀጥለው ዓመት፣ ልክ ከዛሬ አስራ ሁለት ወራት በኋላ፣ የቃል-ኪዳኑ ቀን የተለየ ትርጉም ያለው እንደሆነ ግልጽ ይሆናል። ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤዎች፥ በየአገሮቻቸው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፥ እነዚህን ሁለት ቀናት፥ ተቀራርበው የሚከሰቱ ቢሆንም፥ እያንዳንዳቸው እንዴት እንደሚከበሩ እንዲወስኑ እንጠይቃለን።

እስከዚያ ባለው ጊዜ፣ የብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤዎች እና የክልላዊ ባሃኢ ምክር ቤቶች ተወካዮች በተገኙበት እንደሚከበር ተስፋ ለሚደረገው የአብዱል-ባሃ ዕርገት መቶኛ ዓመት መታሰቢያ ስብሰባ በቅድስት ሀገር እየተደረጉ ያሉት ዝግጅቶች በትጋት ይቀጥላሉ። በተመሳሳይ፥ በጃንዋሪ 2022፥ የተወዳጁ ጌታ ቃለ-ኑዛዜና ኪዳኑ ለመጀመሪያ ግዜ ለሕዝብ የተነበበትን መቶ ዓመት ማለፍን በማያያዝ የአህጉራዊ አማካሪዎችንና የረዳት ቦርድ አባላትን ኮንፈረንስ ለማድረግ ከወዲሁ ዕቅዶች እየወጡ ነው። በእርግጥ፥ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎች፥ በባሃኢ ዓለም ማዕከል ውስጥ ለእነዚህ ስብሰባዎች እየወጡ ያሉ ዕቅዶች ላይ ለውጥ እንዲደረግ ያስገድዱ ይሆናል። ነገር ግን ምንም ይሁን ምን፣ ልክ የአምላክ ጥበቃ በማያከራክር ድንጋጌው መሠረት የታላቁን ዕቅድ መዘርጋት ወደፊት እንደሚገፋው፥ በመላው ዓለም በየአከባቢው ባሉ ማኅበረሰቦች ውስጥ የአብዱል-ባሃን ዕርገት በተገቢው መንገድ ለመዘከርና የቃል-ኪዳኑንም ቀን በዚህ በሚመጣው የመቶ ዓመት መጀመሪያ ውስጥ ክብር ለመስጠት የሚደረጉት ጥረቶች፥ በአምላክ ታናሽ ዕቅድ ተከታይ የሆነውን ደረጃ ለማስጀመርና ስኬታማነቱን ለማረጋገጥ ግፊትን ይሰጣሉ።

በአንድ ዓመቱ ዕቅድ በእያንዳንዱ ተከታታይ ዑደት በእርግጠኝነት እየጨመረ የሚመጣው የእንቅስቃሴ ጉልበት በሁለት ፊልሞች መለቀቅ ኃይሉ የበለጠ ይጨምራል። ከእነዚህ የመጀመሪያው፣ ለመቶኛው ዓመት መታሰቢያው የሚደርስ ሲሆን፣ የአብዱል-ባሃን ስብዕና የሚስል ይሆናል። ለህይወቱ እና ለግብሩ ዝክር ከመሆን ባሻገር፣ በቃላት አጠቃቀሙና በድርጊቱ የሰውን ልጅ አንድነት በልቀት በማሳየት፣ በዘመኑ የነበሩትን መላ-ምቶች እና ጭፍን ጥላቻዎች እንዴት እንደተገዳደራቸውና ብሎም ሊገነባ ለሚፈለገውና እስከ ዛሬ ለቀጠለው የአንድነት ሂደት ግፊትና ንቃት እንዴት እንደሰጠ ይመረምራል። ከመጀመሪያው በኋላ ብዙም ሳይቆይ የሚከተለው ሁለተኛ ፊልም፣ የግንባታውን ዘመን የመጀመሪያ መቶ ዓመታት መደምደም ላይ፥ የባሃኢ ማሕበረሰብ ከወጣበት ከፍታ ላይ ካለው ዕይታ እና ከዚህ ከፍታ ላይ ሆኖ አሁን ለመመልከት ከሚችላቸው አዳዲስ አድማሶች አንፃር፥ የሚያሰላስል ይሆናል።

በዚህ የአንድ ዓመት ዕቅድ ወቅት የሚኖሩት ክንውኖች የላቀ ጠቀሜታ፣ በስብሰቦች ውስጥ የሚከወነውን ሥራ በማጠናከርና ይህንንም ነጠላ ዓመት ቀጥሎ ለሚመጣው ዓለም አቀፍ ሥራ አግባብ ያለው መዘጋጃ በማድረግ ልዩ ባህሪን ያጎናፅፈዋል። ሐሴት በተሞላው የመጠባበቅ ስሜት፣ የባሃኢ ዓለም በሪዝቫን 2022፣ የዘጠኝ ዓመት ዕቅድ እንደሚጀምር እናበስራለን። የሚያስፈልጉት ግብዓቶች እና ድንጋጌዎቹ በቀጣይ የሚገለጹ ይሆናል፣ ነገር ግን የተመደበለት ግዜ ሰፊ ተስፋን እንደሰነቀ ከአሁኑ የማያሻማ ፍንጭ ይሰጣል። እንደ አምላክ ፍቃድ በዓለም ዙሪያ በብዙ ወራት በሚካሄዱ ተከታታይ ስብሰባዎችና ኮንፈረንሶች ይታወጃል።

ይህ፣ አስቀድሞ ሊታይ እስከሚቻልበት ድረስ፣ የባሃኢ ማህበረሰቡ ሊከተለው የሚፈልገው አካሄድ ነው። ለአሁኗ ሰዓት፥ ትኩረታችሁን ከፊት ለፊታችሁ ባሉት ተልዕኮዎች ላይ እንዳደረጋችሁ፥ ጉልበታችሁን ሁሉ እንደገና እንድትሠጡ አጥብቀን እንጠይቃችኋለን። በተለይ ደግሞ የህብረተሰቡ መሠረታዊ የኑሮ ዘይቤዎች በተስተጓጎሉበትና ብዙዎችም የተለያዩ ዓይነት አደጋዎች በተጋፈጡበት በዚህ ወቅት፣ የታላቁ ስም ማህበረሰብ በማንኛውም ሁኔታ፣ በተረጋጋ መንፈስ፣ የመለኮታዊውን መፍትሔ ለማቅረብ ያሳየውን ፍላጎት በማየታችን እጅግ ተደስተናል፡፡ እንዲሁም፣ ወዳጆች በኅብረተሰቡ ጉዳዮች ውይይት ላይ ጎልቶ በሚታዩት ከንቱ ውዝግብ እና ጠብ ውስጥ እንዳይገቡ ወይም - አያድርገውና - የዚህ ዓይነቱ መስተጋብር በፍጥነት፣ በማኅበረሰቡ ውይይቶች ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ ይኖርባችኋል። ነገር ግን በእናንተ በኩል ይህን አለመግባባት ለማስወገድ እና በህብረተሰቡ ውዝግቦች ውስጥ ጠልቆ ላለመግባት የሚደረግ ጥንቃቄ በርካታ ወቅታዊና አሳሳቢ ጉዳዮች እንደማይመለከቷችሁ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም። በጭራሽ ከዚህ የራቀ ነው። እናንተ በጣም ንቁ እና ትጉህ ከሆኑት የሰው ልጅ በጎ ተመኚዎች መካከል ናችሁ። ነገር ግን፣ በድርጊቶችም ይሁን በቃላት፣ ለማህበራዊ ደህንነት የምታበረክቱት እያንዳንዱ አስተዋፅዖ ልቀት የሚገለፀው፥ በመጀመሪያ፥ ተቃራኒ አመለካከቶች ወደ አንድ የሚመጡበትንና ተፋላሚ ሕዝቦች ህብረት መፍጠር የሚችሉበትን ያንን ውድ የሆነ የአንድነት ነጥብ ፈልጋችሁ ለማግኘት ባላችሁ ቁርጠኛ ትጋት ውስጥ ነው።

ከያዝነው የአምስት ዓመት እቅድ ውስጥ፣ በእርግጥም በ1996 ከተጀመሩት እነዚህ ተከታታይ ዕቅዶች ውስጥ፣ ከሁለት ያነሱ ሙሉ ዑደቶች ብቻ ቀርተዋል። በእነዚህ የመዝጊያ ወራት፣ በተቀደሰው ደጀሰላም ላይ በእናንተ ስም ጸሎቶችን እንደምናቀርብ እናረጋግጣለን። እናንተ ለቃል ኪዳኑ ለመሰጠት በልባችሁ በገባችሁት ቃል አማካኝነት፥ በሚማርክ ሁኔታ የምታሳዩትን አንድነት በእጅጉ አጥቶ ግራ በተጋባውና ያለአቅጣጫ በሚንሳፈፈው ዓለም ውስጥ፥ ለእነዚያ ተስፋን የት እንደሚያገኙት ለማያውቁት ተስፋን በመስጠት ስኬታማ እንድትሆኑ እንመኛለን።

ዓለም አቀፍ ቤተፍትሕ